Seattle Office of Economic Development

## ለንግድ መደብር የፊት ገጽታ ደኅንነት ጥበቃ ፈንድ ብቁ የሚሆኑ ኢንቨስትመንቶች

ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ወጪዎች እና ወንጀልን በአካባቢያዊ ዲዛይን መከላከል ፕሮግራም (Crime Prevention through Environmental Design) ሥር ለሚወድቁ ኢንቨስትመንቶች የሚያወጡትን ወጪዎች ተመላሽ ሊያስደርጉ ይችላሉ።

ጥያቄ ለመጠየቅ ወይም በዝርዝሩ ውስጥ ያልተካተቱ ዕቃዎችን መግዛት ፈልገው ብቁ መሆን አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ከፈለጉ፣ እባክዎ ወደ BacktoBusiness@seattle.gov ኢሜይል በመላክ ወይም ወደ (206) 684-8090 በመደወል ይጠይቁ።

- መብራት
- የመስኮት የደህንነት ልጣፍ ፕላስቲክ
- የመስኮት የአበባ መትከያዎች
- "ቢሰበር የማይበታተን" እሽግ መስታወት ያለው መስኮት
- አዲስ የመደብር ታዛ ወይም ለነባሩ ጥገና
- የንግድ ቦታ እና መንገድ መሪ ምልክቶች (ክፍት ነው፣ ዝግ ነው፣ መግቢያ፣ መውጫ፣ የሥራ ሰዓቶች)።
- አድራሻ መሰየሚያ
- በመግቢያ ቦታዎች ላይ የመከላከያ የምድር ገጽታዎች። (የሮዝ ቁጥቋጦዎች / ሆሊ ቡሽ)
- የተፈቀዱ የመንገድ ዳር አበባ መትከያዎች። የመንገድ ዳር ዕቃዎች መመሪያዎቹን ይመልከቱ።
- መቀስ ቅርጽ ያለው የርብራብ ሽቦ በር
- ታጣፊ የርብራብ ሽቦ የመስኮት ደህንነት መዝጊያ
- የበር መቆለፊያዎች
- የመስኮት መቆለፊያዎች
- የማንቂያ/ማስተንቀቂያ ሥርዓቶች (መሣሪያዎቹን ብቻ፣ መቆጣጠሪያ አገልግሎቶቹን እና የደኅንነት ካሜራዎቹን ሳያካትት)
- ጊዜያዊ የመስኮት ወይም በር ማሸጊያ እንጨት
- የመስኮት ጥገና ወይም መተካት ወጪ
- የበር ጥገና ወይም መተካት ወጪ
- የግቢ በር ጥገና ወይም መተካት ወጪ

### ብቁ ያልሆኑ ወጪዎች

- ሕገ-ወጥ የግድግዳ ጽሑፍ ማስወገድ
- የደኅንነት ካሜራዎች ግዢ
- ለደኅንነት ጥበቃ ሠራተኞች የሚደረጉ ክፍያዎች
- የተሰረቁ ዕቃዎች/አገልግሎቶች ካሳ